የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Public Enterprises Holding and Administration Agency

ቀን 07 ታህሳስ 2012
Date
ቁጥር መ24-214/52/01.
Ref. No

በዝርዝሩ ለተመለከቱ የልማት ድርጅቶች
የሥራ አመራር ቦርድ
<u>ባሉበት</u>፤

ጉዳዩ፤ <u>የ40% የትርፍ ድርሻ አጠቃቀም መመሪያን ይመለከታል</u>፤

የመንግስት የልማት ድርጅቶች የሚተዳደሩበት አዋጅ ቁጥር 25/1984 የመንግስት ትርፍ ድርሻ ክፍያን በተመለከተ ማንኛውም የመንግስት የልማት ድርጅት በየበጀት ዓመቱ ከሚያስመዘግበው የተጣራ ትርፍ ላይ ህጉ በሚፈቅደው መሠረት የመጠባበቂያ ሂሳብ (Legal Reserve) ከተነሳ በኋላ የመንግስት ትርፍ ድርሻ የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በሰባት ወራት ውስጥ ገቢ ማድረግ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡

በሂደት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 107/1996 አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የልማት ድርጅቶች የተጣራ ትርፋቸውን በሙሉ ለመንግስት (60% የትርፍ ድርሻ ክፍያ፤ 40% የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ) እንዲያስገቡ በማስቀመጡ እንቅስቃሴያቸውን በብድር ብቻ እንዲያስኬዱ የሚያስገድድ ሁኔታ ተፈጥሮ በመቆየቱ የፋይናንስ ሁኔታቸው አሣሣቢ እየሆነ መጥቷል፡፡ ይህንን በመገንዘብ የትርፍ ድርሻ አከፋፈሉ የድርጅቶችን ቀጣይነት በሚያረጋግጥ አኳኋን እንዲሆን መነሻ ጥናት በኤጀንሲው ተካሂዶ ቀርቦ በገንዘብ ሚኒስቴር ጸድቋል፡፡

በመሆኑም የመንግስት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ በደንብ ቁጥር 445/2011 አንቀጽ (5) ንዑስ አንቀጽ (3) እና (8) በተሰጠው ስልጣን መሠረት ለልማት ድርጅቶች እየተፈቀደ የሚቀረው ትርፍ ለምን ዓላማ፣ በምን ሁኔታ፣ በምን የቁጥጥርና

☎ PBX 251-001-661-09-09
251-011-661-10-45
Fax 011-661-97-34
E-mail :info@pehaa.gov.et
Website www.pehaa.gov.et
✉ 27444-1000(11835)
አዲስ - አበባ - ኢትዮጵያ
Addis Ababa,Ethiopia

ክትትል አሠራር ሥራ ላይ እንደሚውልና ውጤታማ ስለመሆኑም በየጊዜው ክትትል ለማድረግ የሚያስችል "የመንግስት የልማት ድርጅቶች የ40% የትርፍ ድርሻ አጠቃቀም መመሪያ" የተዘጋጀና ከዚህ ደብዳቤ ጋር የተያያዘ ስለሆነ መመሪያው በድርጅታችሁ ከ2013 በጀት ዓመት ጀምሮ ተግባራዊ እንዲደረግ እናስታውቃለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

በየነ ገ/መስቀል ማዳ
ዋና ዳይሬክተር

አባሪ፤ 1 ጥራዝ

ግልባጭ፤

- ለገንዘብ ሚኒስቴር
  አዲስ አበባ፤
- ለኦፕሬሽን ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር
- ለኮርፖሬት ገቨርናንስና ፋይናንስ ስርዓት ዳይሬክቶሬት
  መ.ል.ድ.ይ.አ.ኤጀንሲ፤

ለመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ ተጠሪ የሆኑ ድርጅቶች ዝርዝር

1. የብሔራዊ አልኮልና አረቄ ፋብሪካ
2. የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት
3. የኢትዮጵያ ቱሪስት ንግድ ስራ ድርጅት
4. የፍልውሃ አገልግሎት ድርጅት
5. የግዮን ሆቴሎች ድርጅት
6. የኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን
7. የኢትዮጵያ ግብርና ስራዎች ኮርፖሬሽን
8. የኢትዮጵያ ፐልፕና ወረቀት አ.ማ.
9. የኢትዮጵያ የኮንስትራክሽን ዲዛይንና ቁጥጥር ስራዎች ኮርፖሬሽን
10. የኢትዮጵያ ብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን
11. የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን
12. የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ አገልግሎት ድርጅት
13. የኢትዮጵያ ማዕድን፣ ነዳጅና ባዮፊዩል ኮርፖሬሽን
14. የኢትዮጵያ ስኳር ኮርፖሬሽን
15. የኢትዮ-ቴሌኮም
16. የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት
17. የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ
18. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
19. የኢትዮጵያ ልማት ባንክ
20. የኢትዮጵያ መድን ድርጅት
21. የኢትዮጵያ ንግድ ሥራዎች ኮርፖሬሽን
22. የልማትና ሆቴል ማህበር (አ.ማ.)

የመንግስት የልማት
ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ

የመንግስት የልማት
ድርጅቶች የ40% የትርፍ ድርሻ
አጠቃቀም መመሪያ

502/2013

ታህሳስ 2012 ዓ/ም

አዲስ አበባ

1. መግቢያ

የመንግስት የልማት ድርጅቶች የሚተዳደሩበት አዋጅ ቁጥር 25/1984 የመንግስት ትርፍ ድርሻ ክፍያን በተመለከተ ማንኛውም የመንግስት የልማት ድርጅት በየበጀት ዓመቱ ከሚያስመዘግበው የተጣራ ትርፍ ላይ ህጉ በሚፈቅደው መሠረት የመጠባበቂያ ሂሳብ (Legal Reserve) ከተነሳ በኋላ ከባለሥልጣኑ ጋር በመመካከር የሚወሰነውን የመንግስት ትርፍ ድርሻ የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በሰባት ወራት ውስጥ ገቢ ማድረግ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡

ይሁን እንጂ በሂደት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 107/1996 አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የልማት ድርጅቶች የተጣራ ትርፋቸውን በሙሉ ለመንግስት (60% የትርፍ ድርሻ ክፍያ፣ 40% የኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ) እንዲያስገቡ በማስቀመጡ እንቅስቃሴያቸውን በብድር ብቻ እንዲያስኬዱ የሚያስገድድ ሁኔታ ተፈጥሮ በመቆየቱ የፋይናንስ ሁኔታቸው አሣሣቢ እየሆነ መጥቷል፡፡ ይህንን በመገንዘብ የትርፍ ድርሻ አከፋፈሉ የድርጅቶችን ቀጣይነት በሚያረጋግጥ አካኋን እንዲሆን መነሻ ጥናት ተካሂዶ ለገንዘብ ሚኒስቴር ቀርቦ እንዲጸድቅ ተደርጓል፡፡

በጸደቀው የትርፍ ድርሻ ክፍፍል ፖሊሲ ድርጅቶች በየአመቱ ከሚያገኙት የተጣራ ትርፍ ህጉ በሚፈቅደው መሠረት የመጠባበቂያ ሂሳብ (Legal Reserve) ካስቀሩ በኋላ ከሚተርፈው የገንዘብ መጠን 60 በመቶ ለመንግስት የትርፍ ድርሻ ገቢ እንዲያደርጉ እና ቀሪውን 40 በመቶ ደግሞ በኤጀንሲው በሚዘረጋው ስርአት መሠረት ጥቅም ላይ ማዋል እንዲቻል ወስኗል፡፡

በመሆኑም የመንግስት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ የልማት ድርጅቶች ሊጠቀሙበት የሚችሉትን ቀሪ የትርፍ ድርሻ በምን የአሠራር ሥርዓት ማስተዳደር እንደሚገባ ግልፅ መመሪያ ማዘጋጀቱ ተገቢ መሆኑ ታምኖበታል፡፡ በዚህ መመሪያ መሠረት ለልማት ድርጅቶች እየተፈቀደ የሚቀረው ትርፍ ለምን ዓላማ፣ በምን ሁኔታ፣ በምን የቁጥጥርና ክትትል አሠራር ሥራ ላይ እንደሚውልና ውጤታማ ስለመሆኑም በየጊዜው ክትትል እንዲደረግ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሳዊ ሪፐብሊክ ሚኒስትሮች ምክር ቤት የኤጀንሲውን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን ባወጣው ደንብ ቁጥር 445/2011 አንቀጽ (5) ንዑስ አንቀጽ (3) እና (8) በተሰጠው ስልጣን መሠረት ኤጀንሲው ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የመንግስት የልማት ድርጅቶች የ40% የትርፍ ድርሻ አጠቃቀም መመሪያ" ቁጥር **502/2013** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) **"ኤጀንሲ"** ማለት የመንግስት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ ነው፤

2) **"የመንግስት የልማት ድርጅት"** ማለት በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/84 አንቀጽ 2 (1) የተመለከተውን ትርጓሜ የሚያሟላ ድርጅት ወይም አክሲዮኖቹ ሙሉ በሙሉ በመንግስት ባለቤትነት የተያዙ አክሲዮን ማህበር ሲሆን በሌሎች ሕጎች ወይም በመንግስት ውሳኔ የተለየ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን የተሰየመላቸውን ድርጅቶች አይጨምርም፤

3) **"ቦርድ"** ማለት በአዋጅ ቁጥር 25/84 አንቀጽ 10/2/ እና አንቀጽ 12 መሰረት የመንግስት የልማት ድርጅቶችን በበላይነት እንዲመራ፣ እንዲቆጣጠርና ውሳኔ እንዲሠጥ የተቋቋመ የስራ አመራር ቦርድ ነው፤

4) **"የትርፍ ድርሻ "** ማለት በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ 25/84 አንቀጽ 2(9) መሠረት ከተጣራው ትርፍ ላይ ወደ ሕጋዊ መጠባበቂያ ሂሳብና ሌሎች መጠባበቂያ ሂሳቦች ተቀንሰው 60% የመንግስት ትርፍ ድርሻ ተከፍሎ የሚቀረው 40% ነው፤

5) **“የትርፍ ድርሻ ፖሊሲ”** ማለት የመንግስት የልማት ድርጅቶችን የትርፍ ድርሻ ክፍፍል መጠን ለመወሰን ተጠንቶ በገንዘብ ሚኒስቴር የጸደቀው መመሪያ ነው፡፡

6) **“የትርፍ ድርሻ መጠቀም”** ማለት የልማት ድርጅቶች ከዓመታዊ የተጣራ ትርፋቸው በጸደቀው የትርፍ ድርሻ ክፍፍል ፖሊሲ መሠረት የመንግስትን ድርሻ ፈሰስ ካደረጉ በኋላ ቀሪውን 40% የትርፍ ድርሻ በዚህ መመሪያ ለተፈቀዱ ዓላማዎች በኤጀንሲው ይሁንታ እያገኘ አገልግሎት ላይ የሚውለው ነው፡፡

7) **“የካፒታል ወጪ”** ማለት ቋሚ ንብረት እንደዚሁም የረጅም ጊዜ አገልግሎት ያለው ሥርዓትና ቴክኖሎጂ ለማፍራት ወይም ለማሻሻል የሚደረግ ወጪ ነው፡፡

3. የመመሪያው የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ ለኤጀንሲው ተጠሪ በሆኑ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

ክፍል ሁለት

የትርፍ ድርሻ ክፍፍል እና አጠቃቀም

4. የትርፍ ድርሻ ክፍፍል

4.1. ማንኛውም የልማት ድርጅት ከዓመታዊ የተጣራ ትርፉ ሕጋዊ መጠባበቂያ ሂሣብና ሌሎች መጠባበቂያ ሂሳቦችን በአዋጅ ቁጥር 25/84 አንቀፅ 29 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት ካስቀረ በኋላ 60 በመቶን ለገንዘብ ሚኒስቴር ገቢ ማድረግ ይኖርበታል፤

4.2. በተራ ቁጥር 4.1. የተገለፀው ለገንዘብ ሚኒስቴር ገቢ ሆኖ ቀሪው 40% በሚመለከት የልማት ድርጅቶች ለኤጀንሲው በጥናት ላይ የተመሠረተ ፕሮጀክት እያቀረቡ ሲፈቀድላቸው ጥቅም ላይ ሊያውሉት ይችላሉ፤

4.3. ኤጀንሲው በፅሁፍ ፈቃድ ሳይሠጥ የልማት ድርጅቱ 40% ትርፉን ሊጠቀምበት አይችልም፤

4.4. የትርፍ ድርሻን (40%) ለመጠቀም የሚቀርብ ጥያቄ ከጥናት ሠነድ (የአዋጭነት፣ ወዘተ) ጋር በድርጅቱ ቦርድ ተገምግሞና ፀድቆ በደብዳቤ ሊቀርብ ይገባል፤

4.5. በተራ ቁጥር 4.4. መሠረት ሥራ ላይ የዋለው የትርፍ ድርሻ የድርጅቱን ካፒታል ለማሣደግ ይውላል፤

5. የትርፍ ድርሻ (40%) አጠቃቀም፤

5.1. ድርጅቶች በትርፍ ድርሻ ክፍፍል ፖሊሲ መሠረት እንዲጠቀሙ የተፈቀደውን የትርፍ ድርሻ ለመጠቀም በየበጀት ዓመቱ ዝርዝር ጥናት ለኤጀንሲው አቅርበው መፈቀድ አለበት፤

5.2. ለትርፍ ድርሻ አጠቃቀም የሚቀርበው የልማት ድርጅት ፕሮፖዛል በኤጀንሲው ይሁንታ ካላገኘ የዚያን የበጀት ዓመት የትርፍ ድርሻ 100% /ሙሉውን/ ድርጅቱ ለገንዘብ ሚኒስቴር መክፈል አለበት፤

የልማት ድርጅቶች ... ኤጀንሲ

5.3. የሚፈቀደው የትርፍ ድርሻ በጥናት ላይ ተመስርቶ ለሚቀርቡ የሚከተሉት ዓላማዎች መዋል አለበት፦

1) ለገበያ ማስፋፊያ፤
2) ለምርትና አገልግሎት ማስፋፊያ፤
3) ለምርታማነት አቅም ማሣደጊያ፤
4) ለቴክኖሎጂ ማሻሻያ /ማዘመኛ፤
5) ለአዳዲስ ፕሮጀክቶችና ነባር ማጠናከሪያ ኢንቨስትመንት፤
6) ለምርምር እና ስርፀት ፕሮጀክቶች፤
7) ለብክለት ማስወገጃ፤

5.4. በአንቀጽ 5.3. ላይ ለተጠቀሱ ዓላማዎች ከትርፍ ድርሻ የሚፈቀደው፤ የሚቀርቡ ፕሮጀክቶች አዋጭ ሲሆኑ፣ ፕሮጀክቶቹን ለመፈፀም የሚያስችል አመራር፣ አደረጃጀትና የክትትል ሥርዓት የተዘረጋበትና ተጠያቂነት ያለበት አሠራር መኖሩን ድርጅቶቹ በዝርዝር ሲያሣዩና በኤጀንሲው ሲታመንበት ብቻ ይሆናል፤

6. 40% የትርፍ ድርሻ መጠቀም የማይቻልባቸው ሁኔታዎች፤

6.1. 40% የትርፍ ድርሻ መጠንን ለሚከተሉት ተግባራት ማዋል አይፈቀድም፦

ሀ) ለድርጅቱ ዕለት ተዕለት ሥራ ወይም ለሥራ ማስኬጃ (ለጥሬ ዕቃ፣ ለደመወዝ እና ለልዩ ልዩ ወጪዎች)፤

ለ) ለብድር መክፈያነት /Loan repayment/፤

ሐ) ለመንግስት ግብር እና ታክስ መክፈያነት፤

መ) ኪሳራን ለመሸፈን፤

ሠ) ያልታሰቡ ወጪዎችንና ዕዳዎችን ለመሸፈን፤

ረ) ሌሎች ውጤታማ ላልሆኑ ወይም የሀብት ተመላሽ (Return on investment) ለማያስገኙ ተግባራት፤

6.2. 40% የትርፍ ድርሻን በመጠቀም የተደረጉ የማስፋፊያ ሥራዎች እና የካፒታል ግዥዎች በድርጅቱ የሃብት መግለጫ እና የፋይናንስ ሪፖርት ላይ መታየት ይኖርባቸዋል፤

6.3. ድርጅቶች የትርፍ ድርሻ ተጠቅመው ያከናወኑት የካፒታል ኢንቨስትመንት ያስገኘውን የሀብት ተመላሽ በመተንተንና ንጽጽር በማዘጋጀት (before and after investment) ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ ለኤጀንሲው በቦርድ በኩል ማቅረብ አለባቸው፤

6.4. የትርፍ ድርሻ ገቢን ከታለመለት ዓላማ ውጪ ማዋል ወይም ከሕግ ውጪ ለሌሎች ላልተፈለጉ ተግባራት መጠቀም ወይም መፍቀድ በኃላፊነት ያስጠይቃል፤

6.5. እያንዳንዱ የ40% ትርፍ ድርሻ ተጠቃሚ ድርጅት የፕሮጀክት ሂሳቡን ለብቻ መያዝና በውጭ ኢዲተር አስመርምሮ ፕሮጀክቱ ባለቀ በ6 ወራት ውስጥ ማቅረብ አለበት፤

7. ለትርፍ ድርሻ አጠቃቀም መሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች፤

7.1. የትርፍ ድርሻን በአንቀጽ 5.3. ላይ ለተዘረዘሩት ዓላማዎች መጠቀም የሚቻለው ከታች እንደሚከተለው የቀረቡት ዝርዝር መስፈርቶች ሲሟሉ ነው፡-

ሀ) የልማት ድርጅቱ ሂሳቡን በወቅቱ ዘግቶ በውጭ ኦዲተር ማስመርመሩ እና በወቅቱ ለኤጀንሲውና ለባለድርሻ አካላት መላኩ ሲረጋገጥ፤

ለ) በበጀት ዓመቱ እንዲከፍል የሚጠበቅበትን የመንግሥት ትርፍ ድርሻ ክፍያ በመርሃ ግብሩ መሠረት ገቢ ያደረገና ለኤጀንሲው ያሳወቀ እንደሆነ፤

ሐ) የድርጅቱ የሥራ ባህሪ በሚፈቅደው መሠረት የኢንቨስትመንት የአዋጭነት ጥናት ተዘጋጅቶ በድርጅቱ ሥራ አመራር ቦርድ ቀርቦ በኤጀንሲው ይሁንታ ሲያገኝ፤

መ) ለኢንቨስትመንት የሚያስፈልገውን ገንዘብ በሌላ አማራጭ መሸፈን እንደማይቻል የሚያረጋግጥ ዝርዝር ማብራሪያና መረጃ ድርጅቱ ማቅረብ ሲችል፤

ሠ) የቀረበው የኢንቨስትመንት ጥናት የድርጅቱ ስትራቴጂክ ዕቅድ አካል የሆነ እንደሆነ፤

ረ) ፋይናንስ የሚደረገው ድርጅት/ፕሮጀክት ከመንግስት የፖሊሲ ምርጫና አቅጣጫ ጋር የሚጣጣም ሲሆን፤

8. 40% የትርፍ ድርሻ መጠቀም የማያስችሉ ሁኔታዎች፤

8.1. መንግስት የልማት ድርጅቱን ወደ ግል ባለሃብት ለማዞር በሂደት ላይ ያለ እንደሆነ፤

8.2. የልማት ድርጅቱ የሚያካሂደውን ኢንቨስትመንት በራሱ የገንዘብ አቅም መሸፈን እንደሚችል የሚያረጋግጡ ዕውነታዎች ሲኖሩ፤

8.3. የድርጅቱ ሂሳብ በውጭ ኦዲተር ተመርምሮ የኦዲት አስተያየቱ ዲስክሌይመር /Disclaime Opinion/ ወይም አድቨርስ /Adverse Opinion/ ከሆነ፤

ክፍል አራት

የተለያዩ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

9. የኤጀንሲው ተግባርና ኃላፊነት

9.1. ከልማት ድርጅቶች ትርፍ የሚገኘውን ለበጀት ዓመቱ የተያዘ የመንግሥት ትርፍ ድርሻ የሚከፍሉ ድርጅቶችን እና የሚከፍሉትን መጠን በመለየት እንዲከፍሉ ያደርጋል፤ የገንዘብ ሚኒስቴርና የሚመለከታቸው አካላት እንዲያውቁት ያደርጋል፤

9.2. በየጊዜው ከልማት ድርጅቶች የሚሠበሠበውን የመንግስት የልማት ድርጅቶች የትርፍ ድርሻ ክፍያ አፈጻጸም ይከታተላል፤

9.3. 40% የትርፍ ድርሻ በልዩ ሁኔታ ለካፒታል ማሟያ እንዲጠቀሙ የተፈቀደላቸውን ድርጅቶች አፈጻጸም ይከታተል፤ ይገመግማል፤ ሪፖርት ያዘጋጃል፤

9.4. 40% የትርፍ ድርሻ ክፍያን ለመጠቀም በድርጅቶች የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ተቀብሎ በመመርመር ያፅድቃል፤ ያልተቀበላቸው እንደሆነ ምክንያቱን ያሳውቃል፤

9.5. ድርጅቶች እንዲጠቀሙ የተፈቀደ 40% የትርፍ ድርሻ ክፍያ ለተፈቀደለት አላማ መዋሉን ያረጋግጣል፤ የአጠቃቀም ሪፖርት ድርጅቶቹ በየሩብ ዓመቱና በየዓመቱ እንዲያቀርቡ ያደርጋል፤ ይገመግማል፤ ግብረ-መልስ ይሰጣል፤

9.6. የትርፍ ድርሻ እንዲጠቀሙ የተፈቀደላቸውን ድርጅቶች ዝርዝር እና የተፈቀደውን መጠን በየጊዜው ለገንዘብ ሚኒስቴር ያሳውቃል፤

9.7. የልማት ድርጅቶችን የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት መረጃ ይይዛል፤ ያደራጃል፤

9.8. የኤጀንሲው የኦፕሬሽን ዘርፍ ከላይ ከ 9.1 እስከ 9.7 የተዘረዘሩ ተግባራትን ይፈጽማል፤ ያስተባብራል፤ ሪፖርት ያቀርባል፤

10. የሥራ አመራር ቦርድ ተግባርና ኃላፊነት

10.1. ከትርፍ ድርሻ ለመጠቀም የሚቀርብ የፕሮጀክት ጥናት ደረጃውን የጠበቀ፣ ከስትራቴጂክ ዕቅድና ከመንግስት የፖሊሲ አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ያደርጋል፤ ገምግሞ ለኤጀንሲው ያቀርባል፤

10.2. ከልማት ድርጅቱ የሚጠበቀው የመንግስት ትርፍ ድርሻ በመርሃ ግብሩ መሠረት በበጀት ዓመቱ እንዲከፈል ያደርጋል፤

10.3. የተፈቀደውን የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት በተገቢው ሁኔታ ለመፈፀም የሚያስችል አደረጃጀት፣ አመራር፣ አሠራር እና የክትትል ሁኔታ መኖሩን ያረጋግጣል፤ ለፕሮጀክቱ የተለየ ሂሳብ እንዲኖር ያደርጋል፤

10.4. የፕሮጀክት አፈጻጸሙን ይከታተላል፤ ይገመግማል፤ ሪፖርት ለኤጀንሲው ያቀርባል፤

10.5. የድርጅቱ የፕሮጀክት ሂሳብ በውጭ ኦዲተር እንዲመረመር እና ሪፖርት እንዲቀርብ ያደርጋል፤ በኦዲት ግኝቶች ላይ የማስተካከያ ዕርምጃዎችን ይወስዳል፤ ያስወስዳል፤

11. የልማት ድርጅቶች ማኔጅመንት ተግባርና ኃላፊነት

11.1. ዓመታዊ የተጣራ ትርፍ ግምት መግለጫ ከዘጠኝ ወራት ክንውንና የቀሪ ሦስት ወራት ግምት መነሻ በማድረግ በበጀት ዓመቱ እስከ ሚያዚያ ወር መጨረሻ ድረስ በቦርድ አጸድቆ ለኤጀንሲው ያቀርባል፤

11.2. የልማት ድርጅቱን ሂሳብ በወቅቱ በመዝጋት በውጭ ኦዲተር እንዲመረመር፣ የተመረመረውን ሂሳብ ሪፖርት ለቦርድና ለኤጀንሲው በወቅቱ እንዲደርስ ያደርጋል፤

11.3. ከልማት ድርጅቱ የሚጠበቀውን የመንግስት ትርፍ ድርሻ ክፍያ በተያዘለት ጊዜ በወቅቱ ገቢ ያደርጋል፣ የገቢ ደረሰኙን ኮፒ ለኤጀንሲው ያቀርባል፤

11.4. የመንግስት ትርፍ ድርሻ ከተከፈለ በኂላ ቀሪውን 40% የትርፍ ድርሻ ለመጠቀም ጥያቄውን በቦርድ አማካኝነት ለኤጀንሲው በፅሁፍ ከፕሮጀክት ሠነድ /ጥናት ጋር ያቀርባል፣ ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል፡

11.5. የ40% የትርፍ ድርሻን ለምን ዝርዝር ጉዳይ፣ በምን ያህል መጠንና መቼ ሥራ ላይ እንደሚውል የሚያሳይ መርሃ-ግብር በግልጽ በማስቀመጥ ለቦርድ ያቀርባል፡

11.6. ድርጅቱ እንዲጠቀም የተፈቀደለትን 40% የትርፍ ድርሻ ለተፈቀደለት ዓላማ ብቻ እንዲውል ያደርጋል፡ የአፈጻጸም ሪፖርት በየሩብ ዓመቱና በዓመቱ ማጠቃለያ ለቦርድ እና ለኤጀንሲው ያቀርባል፡

ክፍል አምስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

12. ሪፖርት ስለማድረግ

12.1. 40% የትርፍ ድርሻ እንዲጠቀም ከኤጀንሲው ይሁንታ ያገኘ ማንኛውም የልማት ድርጅት የተፈቀደለትን የትርፍ ድርሻ መጠን ለታለመለት ዓላማ እያዋለ ስለመሆኑ በየሩብ ዓመቱ የአፈጻጸም ሪፖርት ለኤጀንሲው እና እንደአስፈላጊነቱ ለባለድርሻ አካላት ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል፡

12.2. ጥቅም ላይ እንዲውል የተፈቀደው የትርፍ ድርሻ በድርጅቱ የውስጥ ኦዲተር የውስጥ ቁጥጥር እየተደረገበት ሪፖርት ሊቀርብበት ይገባል፡

12.3. ኤጀንሲው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ድርጀቶችን ስለትርፍ ድርሻ አጠቃቀም ተጨማሪ ማብራሪያ ሊጠይቅ ወይም በኦዲተር ሂሳቡ እንዲመረመር ሊያደርግ ይችላል፡

13. ሌሎች ህጎችን ስለማክበር

ከትርፍ ድርሻ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ ያሉ ሌሎች አግባብ ያላቸው ህጎችና ደንቦች መከበር ይኖርባቸዋል፤

14. መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህ መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በኤጀንሲው ሊሻሻል ይችላል፡፡

15. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከታህሳስ 2012 ዓ.ም ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

በየነ ገ/መስቀል

የመንግስት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ